# የህሊና ጉንተላዎች

ቤዝ ፣ አሲምባ ፣ ፀለምት - ጾሎኪያ ፣ ተርናሻ
መሰረት ያኖርኩት - መነሻ መድረሻ
አንዷን ፣ ላውሬ ጥሎ - ሌላዋን ለውሻ
ስደት አድርጎታል - ህይዎቴን መሸሻ።፣

* * * *
እናንት ፣ ወንድሞቼ
እናንት ፣ እህቶቼ
ጠላት አሰፍስፎ - ሰውርና ይፋ
ንቁ ፣ አናንቀላፋ
እኛም ዝምታውን - አበዛነው መሰል
ሁሉም ያነደናል ፣ እንደ ድንጊያ ከሰል ።

* * * *
እንካ ፣ ባለክራር......
ግጥም ፣ ተቀበለኝ
ፍትህ የተጠማሁ - ነፃነት የራበኝ
ዕዝልና አራራይ - አድርገህ አዚመው
ወደ ላይ ፣ ወደ ታች - አንሳውና ጣለው
ቃኘው ፣ ባለክራር......
ቼ- በለው ቼ - በለው
ልቤን ማርከውና - በሙዚቃ አስክረው
በክራርህ ቅኝት - በጣቶችህ ጫፍ ላይ
ስመኝ እኖራለሁ - በህይዎቴ ድል ላይ ።

* * * *
በክፉው ዘመን ወቅት - በዚያ በዘግናኙ
በነፃነት ትግል - ገብተው እየዋኙ
ለተበደሉና ፣ አቅመ ቢስ ፣ ለሆኑት
ጠበቃ እየቆሙ - ህይዎት ለከፈሉት
ነግ ፣ ከነገ ወዲያም - እስከ ዘለዓለሙ
ማስታዎሻ ይሁን - የደም ቀይ ቀለሙ ።

* * * *
የሚተካን ትውልድ - ዐይኑ የታወረ
በዘር ሃረግ ፣ መንገድ - ጥምል እየዞረ
የመንደርተኛ ፣ ቡን - በጎጥ እየጠጣ
ጫት ያመነዥካል - ቅጠል እንደ ጦጣ ።

* * * *
ተማምለን ነበር - ፍፁም ነው ዕምነቴ
ቃልኪዳን ነበረን - ትግሉ ነው ሕይዎቴ

EthioLion.Com

ማተቡን ፈትቶ - ከሃዲ ከዳና
አስገብቶን ጠፋ - በደም ባህር ዋና ።

* * * *
ኢሕአፓ ፣ ሲገደል... .
ለምን ሞተ ፣ ቢሉ
ታሪኩን በነቂስ ፣ ንገሩ ለሁሉ
ያብዮት ዘመቻ ፣ ሞት - ያረገው ስንቁን
የሕዝብ ድርጅት...... ቀይ ሽብር ይልቁን
እርሱን ፣ ብቻ ነበር - ከዜጎቹ አብልጦ
ቋጥሮ የተሸኘው - ኢትዮጵያዊ መርጦ ።

* * * *
አንቺ ፣ የፀደይ አበባ... .
የንቦች ቀሰም ፣ አጥቢያሽ
ፍንድቁ ሲፈካ ፣ ቦራሽ
የፀደይ ጥባቱ ፣ ፀዳል
ጨፈጉ ፈተት - ቧ - ሲል
ለኛ ነጋ ፣ መስከረም ጠባ
አጶዮው ፈካ ፣ ፈነጠቀ
ያንቺው ጀንበር ፣ ግን ጠለቀ ።

* * * *
ሞተዋል ይሉናል - ከሞትን ባገሩ
ህዝቡ ከቀበረን - ከተሜው ገጠሩ
ኢሕአፓ ሲነሳ - የ ‘ሞተ’ አካል ፣ ፈርተው
ቀን ሲደነግጡ - ሌሊት እንቅልፍ ፣ አጥተው
ለምን ይኖራሉ - ዘወትር ባትተው ?

* * * *
ሸበቶውን ዘመን - ግንደ ቆርቁር ፣ ሆኘ
በዘመናት ትግል - በውስጡ ሸፍቼ
ፋሽሽቱን አገዛዝ - ቋያ እሳት ፣ ለኩሼ
በሰደድ - ነበልባል - አመፅ ፣ ተሟግቼ
የዘሩን ዘመን ፣ ግን - እግሬ ነቅሎ ፣ ሂዶ
ሳርር እገፋዋለሁ - ውስጥ አንጀቴ ነዶ ! !

ግንቦት 2002
ABRAHAM BEYENNE

EthioLion.Com

EthioLion.Com